# ልደታ ክፍለከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት የ6ኛ ክፍል የሂሳብ ሞዴል ፈተና

**2016ዓ.ም**

**የጥያቄ ብዛት: 30** **የተፈቀደው ሰዓት: - 1 ሰዓት**

## አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ የሂሳብ ፈተና ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 30 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመመረጥ በመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡ በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡ መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጸዳት አለበት፡፡

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰዓት 1 ሰዓት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኝ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል፡፡
ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት፡፡

## ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !

LIVEWORKSHEETS

<u>ትዕዛዝ፤ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡላቸው አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ብቻ በመምረጥ በተዘጋጀው መልስ መስጫ ወረቀት ላይ አጥቁሩ(C)፡፡</u>

1. ርዝመቱ 9 ሳ.ሜ የሆነ ካሬ ስፋቱ እና ዙሪያው በተከታታይ ስንት ይሆናል?
   ሀ. 36 ሳ.ሜ$^2$ ፣ 81 ሳ.ሜ ለ. 81ሳ.ሜ$^2$፣ 36 ሳ.ሜ
   ሐ. 36 ሳ.ሜ ፣ 81 ሳ.ሜ$^2$ መ. 81ሳ.ሜ፣ 36 ሳ.ሜ$^2$
2. ወ/ሮ አበራሽ ሁለት ባለ 5ሊ በሚይዝ ኮዳ ዘይት ገዛች፡፡ የገዛችውን ዘይት በአንድ ላይ ማስቀመጥ ብትፈልግ ስንት ሜ$^3$ ኮዳ ያስፈልጋታል?
   ሀ. 5000ሜ$^3$ ሐ. 10000 ሜ$^3$
   ለ. 1000ሜ$^3$ መ. 50000ሜ$^3$
3. 9000ሳ.ሜ$^2$ ሬክታንግል ስንት ሜ$^2$ ይሆናል?
   ሀ. 9ሜ$^2$ ለ. 90ሜ$^2$ ሐ. 0.09ሜ$^2$ መ. 0.9ሜ$^2$
4. አቶ ተሾመ ሦስት ሄክታር የእርሻ መሬት ቢኖራቸው ስንት ኪ.ሜ$^2$ የእርሻ መሬት ይኖራቸዋል?
   ሀ. 0.03ኪ.ሜ$^2$ ለ. 0.3ኪ.ሜ$^2$ ሐ. 300ኪ.ሜ$^2$ መ. 3000ኪ.ሜ$^2$
5. ከሚከተሉት ክፍልፋይ ውስጥ ሕገኛ ክፍልፋይ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. $\frac{6}{7}$ ለ.$\frac{10}{10}$ ሐ.3 $\frac{1}{2}$ መ. $\frac{32}{3}$
6. $\frac{8}{4} + 1\frac{2}{4}$ = ……….
   ሀ. $\frac{14}{8}$ ለ.$\frac{14}{4}$ ሐ. $\frac{7}{2}$ መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው
7. ከሚከተሉት ክፍልፋዮች ውስጥ ህገ-ወጥ ክፍልፋይ ያልሆነው የቱ ነው ?
   ሀ. $\frac{6}{7}$ ለ. $\frac{8}{11}$ ሐ. $\frac{8}{8}$ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው
8. $3\frac{3}{4} \times 6\frac{1}{2}$ = ……….
   ሀ. $\frac{195}{8}$ ለ. $18\frac{3}{8}$ ሐ. $\frac{104}{8}$ መ.$\frac{195}{4}$
9. ከሚከተሉት ክፍልፋዮች ውስጥ መቶኛ የሆነው የቱ ነው ?
   ሀ. $\frac{600}{3}$ ለ. $\frac{5}{10}$ ሐ. $\frac{100}{2}$ መ. $\frac{8}{1000}$
10. 0.32 × 1.4 = ………
   ሀ. $\frac{56}{125}$ ለ. $\frac{125}{56}$ ሐ. $\frac{12}{5}$ መ. $\frac{5}{12}$
11. ተማሪ አቤል እስክርቢቶ በስድስት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም ቢገዛ እና ወንድሙ ዮሐንስ በተመሳሳይ በአስራ ሁለት ብር ከስልሳ ሳንቲም ቢገዛ በአጠቃላይ አቤል እና ወንድሙ ለእስክርቢቶ መግዣ ስንት ብር አወጡ?
   ሀ. 18.15 ለ. 19.05 ሐ. 7.51 መ. 19.5
12. 4 ÷ 0.2 = ………
   ሀ. 20 ለ. 40 ሐ.10 መ.2
13. ፍቅርተ ከገዛችው ሰባት ኪ.ግ ቡና ውስጥ ለጓደኛዋ ሦስት ኪ.ግ ቡና ብትሰጣት ፍቅርተ ካላት ቡና ውስጥ ስንት ፐርሰንት ለጓደኛዋ አካፈለች?
   ሀ. 40% ለ. 43% ሐ. 42 % መ. 41%

LIVEWORKSHEETS

14.ተማሪ ኢናያ በሒሳብ ፈተና 24 ከ 30 አመጣች ፡፡ ተማሪ ኢናያ ስንት ፐርሰንት ጥያቄዎችን አጣች?

ሀ. 80%　　ለ. 40%　　ሐ. 20%　　መ.60%

15.444 በብቸኛ ትንትን ሲፃፍ የሚያሳየው የቱ ነው?

ሀ. $2^2 \times 3^1 \times 37^1$　　ለ. $2^1 \times 3^1 \times 37^1$　　ሐ. $2^2 \times 37^1$　　መ. $3^2 \times 37^1$

16. የአንድ ቤት ሆሄው ዜሮ ብቻ ከሆነ ሙሉ ቁጥሩ ለ ……….. ተካፋይ አይደለም ?

ሀ. 3　　ለ. 2　　ሐ. 5　　መ. 10

17. ከሚከተሉት ውስጥ የ 102 አካፋይ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ. 51　　ለ.3　　ሐ. 34　　መ. 12

18. 864 ለ ………. ተካፋይ አይደለም

ሀ. 2　　ለ.3　　ሐ. 9　　መ.7

19. $3^4 \times 2^2 \times 5^1$ በሙሉ ቁጥር ሲገለፅ የሚያሳየው የቱ ነው ?

ሀ. 540　　ለ. 1620　　ሐ. 240　　መ. 162

20. የ $\frac{64}{128}$ በእጅግ ዝቅተኛ ሒሳባዊ ቃል የተገለፀው የቱ ነው ?

ሀ. $\frac{3}{4}$　　ለ. $\frac{5}{6}$　　ሐ. $\frac{2}{3}$　　መ. $\frac{1}{2}$

21. $\frac{4}{5}$ የሚለው ክፍልፋይ በ መቶኛ ሲገለፅ …………. ይሆናል ?

ሀ. 60%　　ለ. 70%　　ሐ. 80%　　መ.50 %

22. 0.731 የሚለው አስርዮሽ በመቶኛ እና በክፍልፋይ በተከታታይ ሲገለፅ….እና….ይሆናል ፡፡

ሀ. 7.31% ፣ $\frac{731}{100}$　　ለ. 73.1% ፣ $\frac{731}{1000}$　　ሐ. 731.0% ፣ $\frac{731}{100}$　　መ. 0.731% ፣ $\frac{731}{1000}$

23. 0.36% ወደ ክፍልፋይ እና አስርዮሻዊ ክፍልፋይ በተከታታይ ሲገለፅ …… እና ……… ይሆናል፡፡

ሀ. 0.36 ፣ $\frac{36}{100}$　　ለ. 3.6 ፣ $\frac{36}{1000}$　　ሐ. 0.0036 ፣ $\frac{36}{10,000}$　　መ. 0.036 ፣ $\frac{36}{10,000}$

24. $\frac{1}{2}$ ፣ $\frac{3}{7}$ ፣ $\frac{9}{7}$ ከ ትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል ሲቀመጥ የሚያሳየው የቱ ነው ?

ሀ. $\frac{3}{7}$ ፣ $\frac{9}{7}$ ፣ $\frac{1}{2}$　　ለ. $\frac{3}{7}$ ፣ $\frac{1}{2}$ ፣ $\frac{9}{7}$　　ሐ. $\frac{9}{7}$ ፣ $\frac{1}{2}$ ፣ $\frac{3}{7}$　　መ. $\frac{1}{2}$ ፣ $\frac{9}{7}$ ፣ $\frac{3}{7}$

LIVEWORKSHEETS

25. ሜላት አንድ ሺ ብር ይዛ ከኤማር ሱፐር ማርኬት $2\frac{1}{2}$ ኪ.ግ ብርቱኳን በ 50 ብር ከ 75 ሳንቲም ፣ $3\frac{1}{4}$ ኪ.ግ ስኳር በ 355ብር ከ 95 ሳንቲም እንዲሁም $4\frac{1}{3}$ ኪ.ግ ኩኪስ በ 99 ብር ከ60 ሳንቲም ብትገዛ ስንት ብር ይቀራታል?

ሀ. 593.7 ለ. 500.7 ሐ. 400.7 መ.493.7

26. $\frac{3}{4}$ + 0.8 = ……….

ሀ. $\frac{31}{20}$ ለ. 1.55 ሐ. 1.555 መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

27. 4.5 ÷ $\frac{2}{5}$ = ………

ሀ. 1125 ለ. 112.5 ሐ. 11.25 መ. መ/አልተሰጠም

28. 12.5 - $\frac{1}{2}$ = ………..

ሀ. 12.0 ለ. $\frac{120}{20}$ ሐ. 12 መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

29. (መ ፣ 168) ት.ጋ.አ 8 ፣ ት.ጋ.ብ 840 ከሆነ የመ ዋጋ ስንት ይሆናል?

ሀ.40 ለ. 56 ሐ. 84 መ. 50

30. የ 28 ፣ 96 እና 204 ት.ጋ .አ እና ት.ጋ.ብ በተከታታይ የተቀመጠው የቱ ነው?

ሀ. 12 እና 84 ለ. 11424 እና 4 ሐ. 4 እና 11424 መ. 84 እና 12

LIVEWORKSHEETS